# ድህረ ምርጫ 2002ና የበቀል ጥቃቶች

## በአንዳንድ የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች

## (ጥንቅር ሁለት) ግንቦት 27/2002 ዓ.ም.

*መቶ ሰዎች ማስፈራሪያና ዛቻ ደረሰባቸው፤ ተሰደቡ፤ ተደበደቡ፤ ታሰሩ፤ ንብረታቸው ወደመ፤ ተዘረፈ፤ ተፈናቀሉ ሲባል የጉዳዩን ክባድነት ሊያሳይ የሚገባው 100 የሚለው አሐዝ ሣይሆን ጥቃቱ በእያንዳንዱ ሰለባና በቤተሰቡ (በህጻናቱ) እና በማህበረሰቡ ላይ በተጨባጭ የሚፈጥረው ቀውስና ጉዳት፤ እንዲሁም የስቃይ የመዋረድና የአለኝታ ማጣት ስሜት ነው።*

### መንደርደሪያ

"ያልተዘገቡ የምርጫ 2002 ሕገወጥ ድርጊቶች - በአንዳንድ የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች" በሚል ርዕሥ አንድ መረጃ-አዘል ጽሁፍ (ጥንቅር አንድ) ከምርጫው ማግሥት መቅረቡ የሚታወስ ነው። ይህ የዚያ ተከታይ መሆኑ ነው። ፈጣሪ ፈቅዶ ሁኔታዎች "በደህና ከሄዱ" ሌሎችም መሰል ጥንቅሮች በማከታተል መቅረባቸው ይቀጥላል። ምክንያቱም የራሳችንንና የግፉአን ወገኖቻችንንም ጩኸት መጮኽ፤ የሌላ ሣይሆን የዓላማና የመርሖ ጉዳይ በመሆኑ ነው።

በጥንቅር አንድ፤ ቅድመ ምርጫ መንግሥታዊ ማስፈራሪያዎችና ማስጠንቀቂያዎች ወደ ተግባር መቀየር መጀመራቸውን የሚጠቁሙ አንዳንድ ምልክቶችን ለማሣየት ተሞክሯል። በዚህ ጥንቅር በዋነኛነት ለማሳየት የሚሞከረው፤ የተደገሱት መንግሥታዊ የቅጣትና የበቀል ጥቃቶች አስቀድሞ በታቀደው መሠረት በድህረ ምርጫም - በተለይ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች ደረጃ - ተስፋፍተው እየቀጠሉ መሆኑን ነው። እንደፊተኛው ሁሉ የዚህኛውም ጥንቅር ከፍተኛ ዓላማ ጉትጎታ ነው። ደረጃውን የጠበቀ ምርመራ ይካሄድ ዘንድ መቆስቆስና ለዚህም በመነሻነት የሚያገለግሉ ጥቆማዎችን ማቅረብና ጭብጦችን ማስያዝ ነው ዓላማው። የተረጋገጡ ሕገወጥ ድርጊቶች በጊዜ በቂ ትኩረት አግኝተው ጠቃሚ በሆነው አግባብ ሁሉና በሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ እንደየሁኔታቸው ሊስተናገዱ ይገባል። ለኢሰብዓዊ ድርጊቶች በጊዜ ዘላቂ መፍትሔ መሻት ተገቢ ነው።

እንደሚታወቀው ገዢው ፓርቲ/መንግሥት ከምርጫው በጣም ቀደም ብሎ ሁሉንም ዓይነት የመንግሥት ዓቅምና መሣሪያ በመጠቀም የፖለቲካውን ምሕዳር መፈናፈኛ - አልባ አድርጎት ነበር። ይህም አልበቃውም ነበር። በምርጫው ክርክርና የቅስቀሳ ዘመቻ ወቅትም ተቃዋሚዎች በሚናገሩትና በሚያደርጉት ላይ ሁሉ ማስረጃ እንደሚያሰባስብ፤ ምርጫው ሲያበቃም መሪዎቹን እንደሚከስና እንደሚያስራቸው በአደባባይ ዝቷል። የዚህ ዓላማው ግልጽ ነበር። የተቃዋሚ መሪዎችን፤ አባሎቻቸውን፤ ደጋፊዎቻቸውንና በአጠቃላይም ሕዝቡን ማሸማቀቅና ፈጽሞ መለጎም ነበር። ይህም አስቀድሞ አስልቶና ሠርቶ የጨረሰውን የመቶ በመቶ አሸናፊነት ዕቅዱን የማረጋገጫ አንድ ተጨማሪ ጥንቃቄና እርምጃ መሆኑ ነው። ዕቅዱ መሳካቱን ያረጋገጠና ሁኔታዎች ሁሉ በቁጥጥሩ ሥር የሆኑ ሲመስለው ደግሞ ለተቃዋሚዎች ምሕረት አድርጌአለሁ አለ። በአደባባይና በመገናኛ ብዙሐን ጭምር የክስ ፋይሉን እንደዘጋ፤ ከምርጫው ጋር በተያያዘ ማንንም እንደማያስር፤ ሁሉንም ወገን በእኩልነት እንደሚንከባከብና እንደሚያገለግል አወጀ። በአሁኑ ሰዓት በተግባር እየታየ ያለው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው።

እዚህ ላይ ቀዳሚ ጭንቀታችን የዜጎች ሕይወት፤ ነጻነት፤ ደህንነትና ንብረት ወዘተ ዋስትና የማጣት ጉዳይ ነው። መጠቃት፤ መገፋት፤ መጨቆን፤ መበዝበዝብ፤ መገለል፤ እንደ ሰውና እንደ ዜጋ ሳይከበሩ፤ በእኩል ዓይን ሳይታዩ፤ በነጻነት ሳይኖሩና ያቅምን ያህል ሳይሠሩ፤ ለውጥ ሳይፈጥሩና ሳያዩ ዕድሜን በድህነት፤ በሥራ አጥነትና በረሀብ በከንቱ መጨረስ - የእነዚህ ሁሉ ጥቃቶች ሰለባ መሆን ለባለጉዳዩ የሚፈጥረውን ጥልቅ የጉዳት ስሜት የሚያውቀው የደረሰበት ነው ልንል እንችላለን። ከዚህ ባለፈ ግን መረጃና ማስረጃዎችን ይዘን፤ የሰለባዎችን ዘርፈ ብዙ ቀውስ፤ ሰቆቃ፤ ጥልቅ የጉዳትና የሕመም ስሜት ለመረዳት፤ "ይህ የደረሰው በኔ ላይስ ቢሆን ኖሮ" ብሎ ለማሰብ መፈለግና መሞከር ይኖርብናል። የሰለባዎችን ህመማቸውን ለመታመም መሞከር ምናልባት ቀጥሎ የሚመጣ ይሆናል። የስሜቱና የምላሹ ደረጃ እንዲህ እያለ እያደገ ይሄዳል፤ መሄድ አለበት።

በዚህ ሂደት ውስጥ ለማለፍ ስንጥር የሚያጋጥመን አንድ የተለመደ እንቅፋት አለ። ይኸውም የሰለባዎችን የስቃይ ስሜቶች እንደሌሉ ያህል ሳያጤኑ በማለፍ ችግሮችን ሁሉ ወደ አሃዝ ደረጃ ዝቅ የማድረግ፤ በአሀዝ ደረጃ ብቻ የመረዳትና የመግለጽ ስህተት ነው። ይህ ቀሊልና ሰው ሰው የማይል የተሳሳተ አተያይና አቀራረብ ነው። ሊስተካከልም ይገባዋል። መቶ ሰዎች ተደበደቡ፤ ታሰሩ፤ ተፈናቀሉ ሲባል ጉዳዩን ከባድ ሊያደርገው የሚገባው 100 የሚለው አሐዝ ሣይሆን ጥቃቱ በእያንዳንዱ ሰለባና በቤተሰቡ (በህጻናት) እንዲሁም በማህበረሰቡ ላይ (ዛሬና ነገ) የሚፈጥረው ተጨባጭ ቀውስ፤ ጉዳት፤ ስቃይ፤ የግራ መጋባትና የተስፋ መቁረጥ ስሜት ነው። የአሁንም ሆነ የወደፊት ሰለባዎችን በአፋጣኝና ከወዲሁ መታደግ ይገባል ስንልም በዚህ መንፈስ ላይ ተመርኩዘን ነው። ይህ ጥንቅርም በዚህ መንፈስ ቢታይ እንወዳለን።



www.debteraw.com

---

በጥንቅር አንድ ማጠቃለያ ላይ፣ በጋሞጎፋ (አርባምንጭ)፣ በወላይታ፣ በዲላ፣ ወዘተ ዞኖችና ወረዳዎች በአጠቃላይ የምርጫው ሒደት ላይ ተመሣሣይ ሕገ ወጥ ተግባሮች መፈጸማቸው ተጠቁሞ ነበር:: በወቅቱ ዝርዝር መረጃዎችን ማግኘትና ማረጋገጥ አልተቻለም ነበር:: ይህ ጥንቅር የሚያተኩረው በነዚህ ዞኖች የተወሰኑ አካባቢዎች ውስጥ በድህረ ምርጫ ተፈጸሙ በተባሉ ሕገወጥ መንግሥታዊ ጥቃቶች ላይ ነው::

## 1ኛ) <u>ጋሞጎፋ ዞን</u>

### 1.1) <u>አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ</u>:

**ሀ) <u>ሳንቴ ቀበሌ</u>**: በአርባ ምንጭ ዙሪያ የሚገኝና ከምርጫ 2002 በፊትም ከፍተኛና ተደጋጋሚ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት የሚፈጸምበት አካባቢ ነው:: መምሕር ብዙነህ ብሩ እና አቶ ስንዝሮ ጌምቦ የሳንቴ ኗሪዎች ናቸው::

1) መምሕር ብዙነህ ብሩ፣ በሳንቴ ምርጫ ጣቢያ የመድረክ የምርጫ ታዛቢ ሆነው ለማገልገል በዝግጅት ላይ ነበሩ:: ነገር ግን ግንቦት 14/2002 ዓ.ም በፖሊስ ከመንገድ ተይዘው ታስረዋል:: ምርጫውንም ሣይታዘቡ ቀርተዋል:: በማግሥቱ እርሳቸው እሥር ላይ እያሉ "በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ያስቀመጠው ቦንብ ተገኘ" በሚል ተወንጅለዋል:: ይህ ጥንቅር እስከሚዘጋጅበት ጊዜ ድረስ ክስ ሳይመሠረትባቸው በአርባ ምንጭ ዙሪያ ፖሊስ ጣቢያ ታስረው ይገኛሉ:: ጉዳዩንና አካሄዱን የተከታተሉና መምሕሩንም በቅርብ የሚያውቋቸው ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ፣ ውንጀላው በገዢው ፓርቲ/መንግሥት አካላት የተቀነባበረ የፈጠራ ውንጀላ ነው፣ መምሕሩ የተቃዋሚ ድርጅት የምርጫ ታዛቢ ለመሆን መወሰናቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው ካልሆነ በስተቀር ሌላ የፈጸሙት ወንጀል የለም ይላሉ::

2) አቶ ስንዝሮ ጌምቦ፣ በሳንቴ ምርጫ ጣቢያ በተቃዋሚ ዕጩ በኩል ምርጫውን ለመታዘብ ተስማምተው በዝግጅት ላይ ነበሩ:: ነገር ግን እርሳቸውም በድምጽ መስጫው ዕለት ዋዜማ ተይዘው ታስረዋል:: ስለዚህ ምርጫውን ሊታዘቡ አልቻሉም:: ይህ ጥንቅር እስከሚዘጋጅበት ድረስም ክስ ሳይመሠረትባቸው በአርባ ምንጭ ዙሪያ ፖሊስ ጣቢያ ታስረው ይገኛሉ::

**ለ) <u>ዘይሴ ወለቃ ቀበሌ</u>**:

3) አቶ ዳዊት ካንኮ
4) አቶ ደረሰ ባርዱ
5) አቶ እንጆሌ ኩሴ

በአርባ ምንጭ ዙሪያ የዘይሴ ወለቃ ቀበሌ ኗሪዎች ናቸው:: ሦስቱም ተቃዋሚዎችን በመወከል ምርጫውን እንዲታዘቡ ተመድበው ነበር:: ነገር ግን ከላይ እንደተጠቀሱት ሁሉ እነርሱም በድምጽ መስጫው ዕለት ዋዜማ ከሕግ አግባብ ውጭ ተይዘው ዘይሴ ላይ ታስረዋል:: እነዚህ ታዛቢዎች ስለታገቱ በተመደቡበት ጣቢያ ድምጽ መስጠቱም ሆነ ቆጠራው እነርሱ ባልተገኙበት ተፈጽሟል:: ሰዎቹ ይህ ጥንቅር እስከሚዘጋጅበት ጊዜ ድረስም በእሥር ላይ ይገኛሉ::

ስማቸው ከታች የተዘረዘረው ስምንት ሰዎችም (ከአንዱ በቀር) የዘይሴ ቀበሌ ነዋሪዎች ናቸው:: ተቃዋሚዎችን በመወከል ምርጫውን በአርባ ምንጭ እንዲታዘቡ ተመድበው ነበር:: ነገር ግን በድምጽ መስጫው ዕለት ከሕግ አግባብ ውጭ ተይዘው በመታሠራቸው ምርጫውን ለመታዘብ አልቻሉም:: በተመደቡባቸው ጣቢያዎች የድምጽ መስጠቱም ሆነ የቆጠራው ሥራ እነዚህ ታዛቢዎች ባልተገኙበት ተፈጽሟል:: ሰዎቹ ለአምስት ቀናት ከታሰሩና ምርጫው ካለፈ በኋላ በግንቦት 20/2002 ዓ.ም. ተፈተዋል::

6) አቶ በላቸው ሶልጋ
7) አቶ ዘርጋ ዓለሙ *(ታዛቢነታቸውን እንዲተዉ ለማስፈራራትና ለማስጠንቀቅ ሲባል በራሳቸውን ወግተው ገድለውባቸዋል)*
8) አቶ ጌቱ አንኤ
9) አቶ አማኑኤል ሽፈራው
10) አቶ ጠጌና ዚዞ

---



www.debteraw.com

11) አቶ አድማሱ ማስታ
12) አቶ እንግሴ ኩሴ
13) አቶ አበበ ቸኮል *(የአርባ ምንጭ የአንድነት/መድረክ ፓርቲ አስተባባሪ ናቸው:: ግንቦት 20/2002 ከተፈቱ በኋላም ከቤታቸው እንዳይወጡ ቤታቸው በፖሊሶች ተከቦ እየተጠበቁ ነው:: ይህ ጥንቅር እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ በቁም እሥር ላይ ናቸው:: በቅርቡም የባለቤታቸውን መሬት ከሕግ አግባብ ውጭ ተነጥቀዋል)::*

### 1.2) <u>ደረማሎ ወረዳ</u> (ጋሞጎፋ ዞን):

ከምርጫው ቀደም ብሎ በደረማሎ ወረዳ መስቃ ቀበሌ ፍሪ የሆኑ የተወሰኑ ሰዎች "ኢሕአዴግን ካልመረጣችሁ ቤታችሁ በድንጋይ ይደበደባል" የሚል ማስፈራሪያና ዛቻ ደርሶባቸው እንደነበር የዚሁ ሕገወጥ ድርጊት ሰለባ የነበሩ ሰዎች ገልጸዋል:: በድምጽ መስጫው ዕለት ደግሞ አቶ ሶቻ ሶራቶ የተባለ የቀበሌው መሬት አስተዳደር ኃላፊ የሆነ ካድሬ ድምጽ በሚሰጥበት ሥፍራ ላይ ተቀምጦ እያንዳንዱ መራጭ ማንን እንደመረጠ ሲቆጣጠርና ሲመዘግብ ውሏል:: በዚህ መሠረት "ንብን" / ገዢውን ፓርቲ ያልመረጡ ናቸው የተባሉ:

1ኛ) የአቶ ተፈራ ታደለ
2ኛ) የወ/ሮ ትዕግሥት ገለሶ መኖሪያ ቤቶች በድንጋይ መደብደባቸውን የተመለከቱ ሰዎች ገልጸዋል::

## 2ኛ) <u>ወላይታ ዞን</u>

በወላይታ ዞን ዳሞት ፉላሣ ወረዳ ውስጥ ከነበሩት የምርጫ ጣቢያዎች መካከል አንደኛው የበቀላ ቀበሌ ምርጫ ጣቢያ ነው:: በመኪና የሚጓዙ የወላይታ ዞንና የዳሞት ፉላሳ ወረዳ ጥቂት ባለሥልጣናት፣ በዚህ ምርጫ ጣቢያ የመድረክ ታዛቢ የነበሩ ሁለት ወጣቶችን በመንገድ ላይ ያገኟቸዋል:: ባለሥልጣኖቹ ወጣቶቹን "ምርጫው እንዴት ነው?" ብለው ይጠይቃሉ:: ወጣቶቹም ምርጫው ተጭበርብሯል ብለው ይመልሱላቸዋል:: በዚህ ምላሽ የተናደዱት ባለሥልጣኖች ወጣቶቹን አስገድደው ወደቀበሌው በመውሰድ አስደብድበዋቸዋል:: ቀጥለውም ለፖሊስ በማስረከብ አስረዋቸዋል:: ይህ ጥንቅር እስከሚዘጋጅበት ጌዜ ድረስ ወጣቶቹ በዳሞት ፉላሳ ወረዳ በሻንቶ ፖሊስ ጣቢያ በሕገወጥ መንገድ ታስረው ይገኛሉ::

## 3ኛ) <u>ጌዴዖ ዞን</u> (ዲላ)

1) አቶ አክሊሉ ታደሰ በዲላ ከተማ በ02-ለ ምርጫ ጣቢያ የመኢአድ ታዛቢ የነበረ በምርጫው ዕለት ወደ ምርጫ ጣቢያው እንዳይገባ ተከልክሎ ሳይታዘብ ተመልሷል::
2) አቶ ምኒልክ ጌታሁን በዲላ ምርጫ ክልል የመኢአድ ተዘዋዋሪ ታዛቢ የነበረ በምርጫው ዕለት ፖሊሶች ደብድበው እንዳይታዘብ አባረውታል::
3) አቶ ኑሪ ረጅቦ (የመኢአድ ታዛቢ የነበረ) እና አቶ ብርሐኑ ታደሰ የመኢአድ አባል የሆነ በምርጫው ላይ ከነበራቸው ተሣትፎ ጋር በተያያዘ ሁለቱም በ18/09/2002 በፌዴራል ፖሊስ አባሎች ተደብድበዋል::

## 4ኛ) <u>ሀዋሳና አካባቢው</u>

1) በሀዋሳ ምርጫ ክልል የተቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች ጠቅላላ ቁጥር በትክክል አይታወቅም ነበር:: የሀዋሳ ምርጫ ክልል ምርጫ አስፈጻሚ ጽ/ቤት በሥሩ ያደራጃቸውን የምርጫ ጣቢያዎች ብዛት እንዲያሳውቃቸው በተቃዋሚዎች በደብዳቤና በቃል ቢጠየቅም ትክክለኛ መረጃ በጊዜ አልሰጣቸውም:: በምርጫ አስፈጻሚው ሚስጥራዊነት ጥርጣሬ ያደረባቸው ተቃዋሚዎች በግላቸው ባደረጉት ክትትል በሀዋሳ ከተማ ብቻ 22 የምርጫ ጣቢያዎች በድብቅ እንደተቋቋሙ የደረሱበት መሆኑን ገልጸዋል:: ከዚህ በመነሣት በሌላም አካባቢዎች ለተቃዋሚዎችና ምናልባትም ለሁሉም መራጮች ያልተገለጹ ተመሣሣይ የድብቅ ምርጫ ጣቢያዎች ሳይቋቋሙ እንዳልቀሩ ያምናሉ:: ተቃዋሚዎች ይህ የድብቅ አሠራር በነዚህ ምርጫ ጣቢያዎች ታዛቢዎቻቸውን በጊዜ ለመመደብ እንዳላስቻላቸውና ሌላም ለጊዜው ገና ያላረጋገጡት ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርስባቸው እንዳልቀረ ይገምታሉ::



www.debteraw.com

2) ተቃዋሚዎች ለታዛቢነት የመደቧቸውን ሰዎች ጠቅላላ የስም ዝርዝር በማጣደፍና በማስጨነቅ እንዲያቀርቡ በምርጫ አስፈጻሚዎች መገደዳቸውን ይገልጻሉ። የታዛቢዎች ማንነት ከታወቀ በኋላ የገገርው ፓርቲ ካድሬዎች "የሐገር ሽማግሌ" በሚባሉ ሰዎችና በቀበሌዎች ረዳትነት፣ "መጠነ ሰፊና ለመቆጣጠር እንኳን ያዳገተ" ያሉትን የማስፈራራት ዘመቻ በተቃዋሚ ታዛቢዎች ላይ እንዳደረጉባቸው ተቃዋሚዎች ይገልጻሉ። በዚህም የተነሣ በርካታ ታዛቢዎች በድምጽ መስጫው ዕለትና ጣቢያ ሳይገኙ ቀርተዋል።

3) በሁሉም የሀዋሳና ዙሪያው ምርጫ ጣቢያዎች የተመደቡት የቦርዱ የምርጫ አስፈጻሚዎችና የሕዝብ ታዛቢ የተባሉት በድምጽ መስጫ ሥፍራዎች ተገኝተው ሥራቸውን የጀመሩት የተቃዋሚዎች ታዛቢዎች ባልተገኙበት (ግንቦት 14) ከሌሊቱ 9 ሰዓት እንደነበር ተቃዋሚዎች ይገልጻሉ።

4) እያንዳንዱ መራጭ በድምጽ መስጫ ኮሮጆ ውስጥ መጣል የሚኖርበት የድምጽ መስጫ ወረቀት ብዛት ሁለት ብቻ ነው (አንድ ለፌዴራል ፓርላማ አንድ ለክልል ምክር ቤት)። ሆኖም አራቱ በአንድ ላይ እየተደረጉ ተጠቅልለው ኮሮጆ ውስጥ የተጨመሩ 6 የድምጽ መስጫ ወረቀቶች (6 x 4 = 24) በአንድ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ ተገኝተዋል። ይህም የተደረሰበት በድምጽ ቆጠራ ወቅት በአንድ የመኢአድ ታዛቢ አማካኝነት ነው። ታዛቢው በጉዳዩ ላይ ጥያቄና ተቃውሞ ሲያነሳ በሥፍራው የነበሩት የምርጫ አስፈጻሚዎችና ካድሬዎች ወዲያውኑ አባረውታል ተብሏል።

5) እንደ ሌሎቹ የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ሁሉ በሀዋሳ፣ በቱላና በጉጉማ ምርጫ ክልሎችም ውስጥ የተካሄደው የተቃዋሚዎች የቅድመ ምርጫ፣ የምርጫ ወቅትና የድህረ ምርጫ እንቅስቃሴ በአብዛኛው በተጽዕኖ፣ በወከባ፣ በእንግልትና በእሥራት የታጀበ እንደነበረ በሀዋሳ ቆይታ አድርጎ የነበረው ተባባሪያችን አመልክቷል።

## <u>ሲዳማ ዞን</u>

### ሀ) <u>ቦናያ ሚሪዴ ቀበሌ</u> (ሸበዲኖ ወረዳ):

በምርጫው ማግሥት (16/09/2002) በሸበዲኖ ወረዳ ቦናያ ሚሪዶ ቀበሌ የ16 ሰዎች መኖሪያ ቤቶች በደኢህዴን/ኢሕአዴግ አባላትና ታጣቂዎች ተደብድበው ከፍተኛ ጉዳት ደርሦባቸዋል። የዚህ ጥቃት ሰለባ የሆኑት ዜጎች "የሲዳማ ሐዲቾ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት" የተባለ ተቃዋሚ ቡድን ዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች ናቸው። ከድርጅቱ አመራር አባላት እንደተሰማው ከሆነ ጥቃቱ የደረሰባቸው፣ "ለምን ኢሕአዴግን ተቃውማችሁ ተወዳደራችሁ? ለምን ደኢህዴን/ኢሕአዴግን ትታችሁ ሌላ መረጣችሁ?" በሚል ነው። ከጥቃቱም በኋላ አካባቢያቸውን ለቀው እንዲሄዱ ማስፈራሪያ ስለደረሳቸው ሸሽተውና ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው በሌላ አካባቢ ተጠግተው እንደሚገኙ ተገልጿል።

### ለ) <u>ዶቤ ነጋሽ ቀበሌ</u> (ሸበዲኖ ወረዳ):

በግንቦት 17/2002 ዓ.ም. የዚሁ "የሲዳማ ሐዲቾ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት" 11 አባላትና የምርጫ ታዛቢዎች መኖሪያ ቤቶች ላይ ከፍተኛ ጥቃት እንደተፈጸመ ተገልጿል። ባህር ዛፎቻቸው ተቆራርጠዋል፣ የግቢዎቻቸውን አጥር በማፈራረስ በአህያ ጭነው ወስደውባቸዋል። የዚህ ጥቃት ሰለባዎች የሚከተሉት ናቸው፡

1) አቶ ዳንኤል ሀርሶ
2) አቶ ቃናጥር ቃማቶ
3) አቶ ንጉሤ ሀርሶ
4) አቶ ለገሠ ሳሊሞ
5) አቶ ሳሙኤል ደበላ
6) አቶ ካሡ ከልባታ
7) አቶ ደምሴ ደበላ
8) አቶ ኤልያስ ሳምሶ
9) አቶ ቶማስ ዳንኤል



www.debteraw.com

10) አቶ እሥራኤል ዳማ
11) አቶ እንባቆም ቃማሴ

በነዚህ ዜጎች ላይ ይህንን ሕገወጥ ድርጊት ፈጸሙ የተባሉት ሰዎች 1ኛ) ማቴዎስ አማሎ 2ኛ) ላቶ ደምሴ 3ኛ) ሕርዳ ደራጎ 4ኛ) ማጁላ ደንጋፎ 5ኛ) አዳላ ቦርዴ 6ኛ) ባንዶ ዳቲ 7ኛ) ታሎ 8ኛ) መንቃ ላንቃሞ 9ኛ) ዘመቻ 10) ዳቤ ሹራሞ 11) ሳጉላ ኩማ 12ኛ) ምንዳ ምልክያስ የሚባሉ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎችና ታጣቂዎች መሆናቸውም ታውቋል፡፡


## ሐ) <u>ሞርቾ ሸንደሞ ቀበሌ</u> (ሸበዲኖ ወረዳ)፡

በሞርቾ ሸንደሞ ቀበሌ ኗሪ የሆኑት አቶ አማን ዳሌ፣ በምርጫው ወቅት ተቃዋሚውን የሲዳማ ሐዲቾ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ደግፈው በመቆማቸው ብቻ ጥቃትና ከፍተኛ የንብረት ውድመት እንደደረሰባቸውም ተገልጿል፡፡ ጥቃቱን ያደረሰባቸው አቶ መሰይድ ቃቃሽ የተባለ የገዢው ፓርቲ ካድሬ ከታጠቁና ካልታጠቁ ተባባሪዎቹ ጋር በመሆን ነው፡፡ በጥቃቱ አቶ አማን ዳሌ በርካታ የእንሰት፣ የቡናና የበቆሎ ተክሎች ተጨፍጭፈው ከጥቅም ውጭ ሆነውባቸዋል፡፡

የድርጅቱ አመራሮች እንደሚሉት፣ ድርጅቱ በሚንቀሳቀስባቸው ሌሎች ወረዳዎችና ቀበሌዎችም ውስጥ በሚኖሩ አባልና ደጋፊዎቻቸው ላይ በርካታ ተመሣሣይ ጥቃቶች ተፈጽመውባቸዋል፣ እየተፈጸመባቸውም ነው፡፡ እስካሁን ተጨባጭና አጥጋቢ ምላሽ ባያገኙም ስለችግሩ ለሚመለከታቸው የክልሉና የዞኑ ኃላፊዎች አቤት ብለዋል፡፡ በመሆኑም የኑሮ ዋስትና አጥተው ተፈናቅለውና ተደብቀው ከነቤተሰባቸው በጥገኝነት በመሰቃየት ላይ ለሚገኙት፣ ቤት-ንብረት ለወደመባቸውና አሁንም ማስፈራሪያና ዛቻ እየደረሰባቸው ለሚገኙት አባላትና ደጋፊዎቻቸው ሁሉ የሕግ ጥበቃ እንዲደረግላቸው፣ ፍትሕ እንዲሁም የንብረትና የሞራል ካሣ እንዲያገኙ፣ የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ እንዲደረግላቸው፣ ጥቃት ፈጻሚዎቹም በሕግ እንዲጠየቁላቸው የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ ትብብር እንዲያደርጉላቸው አበክረው ጠይቀዋል፡፡



www.debteraw.com



**በወያኔ የቧልት ምርጫ ዕለት ለገዢው ፓርቲ አባላት በቅድሚያ ተሰጥተው እና ንብ መሰሏ ዝንቦ ላይ ምልክት ተደርጎባቸው ለማጭበርበሪያ ተዘጋጅተው እጅ ከፍንጅ የተያዙ የምርጫ ወረቀቶች**

